
# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

## ፰



ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ.ም.

**ርእሰ አንቀጽ ።**

# ለተሟላ ኑሮ የተሟላ ምርት

በሀገራችን ለረዥም ጊዜ የቆየው የፊውዳል ሥርዓትና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጫነበት ኢምፔሪያሊዝም ተጣምረው የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝቦች ከዓለም ወደር የማይገኝለት የቀረቀዘና የተጕሳቀለ ኑሮ ላይ ተንጠልጥለው ፍዳቸውን እንዲቆጥሩ አርጓቸዋል ።

ይህ የፊውዶ ካፒታሊስት ሥርዓት የሀገራችን የሰው ጉልበትና የተፈጥሮ ሀብት በሚገባ ከሥራ ላይ ውሎ ምርት እንዳይዳብር አፍኖ ይዞ ነበር ። የምርት ኃይሎች እጅግ ወደኋላ እንዲቀሩ ከማድረጉም በላይ በነዚህ ወደኋላ በቀሩ የምርት ኃይሎች አማካይነት የሚመረተው ከእጅ ወደአፍ እየሆነ የኑሮ ጠርዝ ላይ የሚያንጠለጥል እንጂ ለሰፊው ሕዝብ በምንም ዓይነት የሚያዝናና አልነበረም ።

ይህ ሥርዓት ምርትን ከማቀርቀዙም በስተቀር በምርት ክፍያም አንፃር ሲታይ እጅግ ግፈኛ ሥርዓት ነበር ። የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች የቀን ሐሩር የሌሊት ቍር ሳይበግራቸው ለፍተው ከሚያመርቱት ሁሉ አብዛኛውን እጅ ተቀምጦ ለሚበላው የፊውዳል መደብ እያስረከቡ በገዛ ሀገራቸው ፤ በገዛ ምርታቸው የበይ ተመልካች ሆነው እንዲዋረዱ ያደረጋቸው ሥርዓት ነበር ።

እጅግ ዝቅተኛ የምርት ውጤት እጅግ ግፈኛ የምርት ክፍፍል ፤ የኢትዮጵያን ጭቁኖች በረኃብ ሰንሰለት አሥሮ በበሽታ አውተብትቦ ፤ በድንቁርና ጨለማ አፍኖ ከዓለም ሕዝቦች ሁሉ የተበዘበዙና ወደ ኋላ የቀሩ ያደረጋቸው የፊውዶ ካፒታሊስት ሥርዓት የኢኮኖሚ ዓይነተኛ መልኩ ይኸው ነበር ። ሀገራችንም ለረጅም ዘመናት የጥቂቶች ጠግቦ መትረፍረፍ ፤ የብዙኃን በረኃብ አለንጋ መገረፍ ፤ የጥቂቶች መብለጭለጭና የብዙኃን መራቆት ፤ የጥቂቶች የተሟላ የኑሮ ፍሥሐና የብዙኃን የኑሮ ፈተና ከየትም ይልቅ ዓይን አውጥተው የተዳበሉበት የግፍና የጨለማ አገር ሆና ቆይታለች ።

ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ይህን ውርደትና ይህን ብዝበዛ አሜን ብሎ የተቀበለበት ጊዜ አልነበረም ። እየወደቀና እየተነሣ ፤ እየተዳፈነና እየተቀጣጠለ የተጠራቀመው አብዮታዊ ትግል በየካቲት ወር ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ፈነዳ ። የኢትዮጵያ ጭቁኖችም በዚህ ብዙ መሥዋዕትነትና መከራ በተቀበሉበት ታሪካዊ ተጋድሏቸው ያ የጨለማና የውርደት ሥርዓት አንገፍግፏቸው ለአዲስ ሕይወትና ለአዲስ ኑሮ ቆርጠው እንደተነሡ አሳዩ ። ይህም ቆርጠው የተነሡለት አዲስ የኑሮ ሥርዓት በሰላም ፤ በአንድነትና በነፃነት በትግላቸውና በወዛቸው ምርታቸውን እያዳበሩ ፤ ከዚህም እያደገ ከሚሄድ ምርታቸው ለእያንዳንዱ እንደየሥራው የሚከፈልበት ሕዝባዊ ሥርዓት ለመመሥረት የሚቻልበት ነው ።

ይህንን ደግሞ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ከማንም በምጽዋተኛነት አይጠብቁትም ። ከማንም በጎ አድራጊ የሚለገሡት ችሮታም አይደለም ። በትግሉ ነፃነቱን የተጐናጸፈው ሰፊው የኢትዮጵያ



ሕዝብ ለለምለምና ለሀብታም አገሩ ወዙን እያንጠፈጠፈ አሁንም በትግል የሚገነባው የኑሮ ፍሥሐ ነው ።

ይሁን እንጂ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለተሟላ ኑሮ የሚያደርገው ተጋድሎ ጨቋኞቹን ገርስሶ የጣለለት አያከትምም ። ነፃነት አንድን ሕዝብ ከብዝበዛ ቀንበር አላቆ የወደፊት ዕድሉን ቁልፍ ያስጨብጠዋል እንጂ ሌላ የሚጨምርለት ተአምር የለውም ። አንድ ሕዝብ ከብዝበዛ ስለተላቀቀ ብቻ ከሰማይ መና እየወረደለት አይኖርም ። የተሟላ ኑሮ ለመኖር ሌሎች ነፃ ሕዝቦች በተጓዙበት ለነፃነቱ ካደረገው ተጋድሎ በምንም በማያንስ ታታሪነት ፤ ታጋይነትና መሥዋዕትነት ፤ የዚያኑ ያህል መንፈስ ጠንካራነትንና ዲስፕሊንን በሚጠይቀው የማምረት ጐዳና ላይ መሠማራትና በዚህም ግንባር ሌት ተቀን መግፋት ይኖርበታል ።

ባጭሩ አንድ ሕዝብ በዝባዦችንና ጨቋኞችን በመደምሰሱ ብቻ የተሟላ ኑሮ አይኖርም ። ለተሟላ ኑሮ ነፃ አገር ብቻ ሳይሆን ፤ የተሟላ ምርትና የተስተካከለ ክፍያ ያስፈልጋል ።

ከላይ እንደተጠቆመው ባለፈው ግፈኛ ሥርዓት ውስጥ ለኢትዮጵያ ጭቁኖች መታረዝና መዋረድ አንዱ ምክንያት የሰፊው ሕዝብ ወገኖች የወዛቸውን ፍሬ መነፈጋቸውንና የጨቋኙ መደብ አባሎች ካላፈሩት ምርት አብዛኛውን እጅ እየዛቁ እንዲትረፈረፉበት መደረጉ ነበር ። ይህንን የመትረፍረፍ ሁኔታ በደመወዝ ስኬልም ብንመለከተው የባሰ ሆኖ እናገኘዋለን ። ለምሳሌ ያህል በበዝባዡ መደብና በወዝአደሩ መደብ መካከል ያለው የደመወዝ ዓይነት ፪፻ ጊዜ እጥፍ እንደነበረ እናያለን ።

በመሠረቱ የደመወዝ ልዩነት አይኑር አይባልም ። እንኳን አሁን ባለንበት የመሸጋገሪያ ዘመን ይቅርና በሶሻሊስት ኅብረተሰብ እንኳን የሚኖር ነገር ነው ። በዚህ በኩል የሶሻሊዝም መርህ የታወቀ ነው ። በመጀመሪያ <u>«የማይሠራ አይብላ» ስለሚል</u> ተቀምጦ ለመብላት የሚፈልገውን በዝባዥ በኅብረተሰቡ ውስጥ ቦታ ይነፍገዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ አድኃሪዎችና አናርኪስቶች እንደሚያናፍሱት ከምርቱ ሁሉም እኩል ይካፈላል ማለት አይደለም ። በዚህም በኩል የሶሻሊዝም መርህ የታወቀ ነው ። <u>«ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው»</u> ይላል ። እያንዳንዱ ግለሰብ ከኅብረተሰቡ ምርት የሚያስፈልገውን ሁሉ እንዳስፈለገው እየወሰደ የሚዝናናበት ሥርዓት የኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበር ብቻ እንደሆነ እነማርክስ ግልጥልጥ አድርገው ያስተማሩት ነገር ነው ። በዚህ ሥርዓተ ማኅበር ብቻ ነው ኅብረተሰብ ምርቱን ከመጠን በላይ በተትረፈረፈ ሁኔታ አሳድጎ <u>«ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደፍላጐቱ»</u> የሚለውን የኮሚኒዝም ባንዲራ የሚያውለበልበው ።

በሀገራችን እጅግ አጣዳፊ የሆነው የደመወዝ መስተካከል ጉዳይ መታየት ያለበት ከዚህ በላይ በጠቀስናቸው ሃሳቦች አንፃር መሆን ይገባዋል ። በደመወዝ ክፍያ ጉዳይ ካለፈው ሥርዓት የወረስነው ኢሰብአዊ የሆነ ሁኔታ ዛሬም ተቆራኝቶን እንደሚገኝ ግልጽ ነው ። የደመወዝ መስተካከልም ጉዳዩ የአብዮታችን አንድ ዋና ጥያቄ ሆኖ የቆየውም ለዚሁ ነው ።

የኢትዮጵያ ወዝአደር የአብዮቱ አመራር ታሪካዊ ኃላፊነት የጣለበትና የአብዮቱ ድል ባለቤት እንደመሆኑ መጠን በዚህ በትግልና በመሸጋገሪያ ጊዜ ብዙ መሥዋዕትነት እንደሚጠበቅበት ያው

ቃል ። በመሠረቱ የኢትዮጵያ ወዛደር ለኑሮ ችግሩ ዘላቂ መፍትሔ የሚያገኘው እስከዚህም ደመወዝ በመጨመር ላይ በማተኮር እንዳይደለ ግልጽ ነው ። ቋሚ መፍትሔ ለማግኘት በመጀመሪያ ነቅቶ ፤ ተደራጅቶና ታጥቆ የገዛ ዕድሉን እጁ ማስገባት እንዳለበት ፤ ከዚህም ጋር አጣምሮ ምርቱን ማሳደግና ፍትሕ የሰፈነበት የምርት ክፍያ ዘዴ ያለበት ሥርዓት ሲመሠርት ብቻ ነው ። በሌላ በኩል ግን በዚህ በመሸጋገሪያ ወቅትም ቢሆን ወዝአደሩ ካለፈው ሥርዓት ከተወረሰው ኢሰብአዊ ከሆነው የደመወዝ አዘቅት ወጥቶ ትንሽ ፋታ የሚሰጥ ኑሮ የሚኖርበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት የማይታበል ሀቅ ነው ።

ጥያቄው ምን ያህል ጭማሪ የሚለው ነው ። የሚደረገውን ጭማሪ መንግሥት ከፈለገ ሰማይ ሊያስጠቅሰው ፤ ከፈለገ ደግሞ መሬት ሊቀብረው የሚችለው ነገር እንዳይደለ ግልጽ ነው ። በመሠረቱ ደመወዝ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ የመክፈል አቅም ላይ መመርኮዝ አለበት ። በሀገሪቱ ከሚመረተው ሀብት ጋር መመጣጠን አለበት ። ምርት የማይመጣጠነው ጭማሪ ሰማይ ቢጠቅስ የዕቃ ዋጋ ደግሞ ሰማይን ጥሶ ይወጣል ።

ትላንት ወዝአደሩን የደም ዕንባ ሲያስለቅሱትና እስከአጥንቱ ሲግጡት ትንሽም ያልሳሱለት አድኃሪዎች ዛሬ «ከአብዮቱ ምን አገኘህ» እያሉ በጆሮው ሹክ እንደሚሉት ሁሉ ነገ ደግሞ የመጣ ጭማሪ ቢመጣ «ይቺ ከምኑ ጠብ ትላለች አነሰኝ በል» እያሉ መወትወት እንደሚጀምሩ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው ። በሀገሪቱ ኢኮኖሚ አቅም ላይ ተመርኩዞ የሚመጣውን ጭማሪ አሻጥረኛው ነጋዴ በዋጋ ጭማሪ ሊበላው እንደሚያደባም የማያጠራጥር ነው ። የአብዮቱ ግስጋሴና ድሎች ምን ያህል እንደጎዱቸው ጠንቅቀው የሚያውቁ አድኃሪያን በዚህ በኩል ወዝአደሩ በትግሉ የሚጐናጸፈውን ድል ለማንቋሸሽ ለማቃለል እንደሚፍጨረጨሩ ካሁኑ ልንጠብቀው የምንችለው ጉዳይ ነው ።

ነገር ግን የኢትዮጵያ ወዝአደር ዛሬ በደረሰበት የንቃት ደረጃ የተሟላ ኑሮው ከነፃነቱና ከተሟላ ምርት ጋር የተያያዘ መሆኑን ያውቀዋል ። የደመወዝ መስተካከል ጉዳይ ከአጣዳፊ ችግሮች ለመላቀቅና ፋታ ለማግኘት እንጂ ዘላቂ መፍትሔ እንደማይሆነው ያውቃል ።

ዘላቂው መፍትሔ አብዮታዊ ትግሉን ማፋፋም ፤ በታታሪነትና በዲስፕሊን በማምረት ግንባርም አዲስ የትግል ምዕራፍ መክፈትና በዚህም አንፃር ያለማቋረጥ መግፋት ብቻ እንደሆነ ከእኛ በፊት አብዮታቸውን ያካሄዱ ሕዝቦች ታሪክ የሚያስተምረን ሀቅ ነው ። ምርትን የማሳደግ ጉዳይ የአብዮታዊ ትግላችንና የተሟላ ኑሮዋችን የማይነጠል አካል በመሆኑ በዚህም በኩል በታታሪነትና በዲስፕሊን አዳዲስ ምዕራፎችን እየከፈቱ ወደፊት መራመድ ያስፈልጋል ። ዘላቂው መፍትሔ ይኸው ነው ።

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው
አብዮታዊት ኢትዮጵያ